42ኛው የህወሓት ምስረታ በዓል በቤጂንግ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች፣ እንዲሁም የኤምባሲው ሠራተኞችና የኮሚኒቲ አባላት በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል፡፡ በዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉት በቻይና የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደርና የህወሓት መስራች ታጋይ ስዩም መስፍን የትግሉን እልህ አስጨራሽነትና የተከፈለውን መስዋዕትነት አስታውሰው ለተሳታፊዎቹ አብራርተዋል፡፡



ህዝባዊ ዓላማ ያነገቡ ጥቂት ግለሰቦች የመሠረቱት የትግል መስመር ከሌሎች የአገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦች ድርጅቶች ጋር በጋራ በመታገል በአገራችን ተንሰራፍቶ የቆየውን ጨቋኝ ሥርዓት በመገርሰስ መላው የአገራችን ህዝቦች የዴሞክራሲ ጮራ እንድፈነጠቅላቸው ጉልህ ድርሻ የተወጡ በመሆናቸው በታሪክ አጋጣሚ የሥራ ባልደረባ መሆን ያስደሰታቸው መሆኑን በመግለጽ የኤምባሲው ሰራተኞች ለክቡር አምባሳደር ስዩም መስፍን ሽልማት አበርክተውላቸዋል፡፡ በበዓሉ ላይ በትግል ወቅት ይዘፈን የነበረው የፅናት መዝመር ተዘምሯል፡፡

